# እኔን በእሱ አሳየኝ

## ከአንሙት

ከዕለታት አንድ ቀን፣ ለቱርጅማንነት ተጠርቼ ሥራ፣
ካስተረጎምኩለት፣ የሀገሬ ሰው ጋር፣ በሰፊው ሣወራ፣
"ካገር እንዴት ወጣህ?" ብዬ ስጠይቀው፣
እንደዚህ በማለት ታሪኩን ጀመረው፣
"የተማረው ሁላ፣ ከተማውን ጥሎ፣
"ከጫካ ሲገባ፣ ዱሩ ጥራኝ ብሎ፣
"ከዚያ የተሻለ፣ ቢገኝ ነው ብዬ፣
"ሞፈሬን፣ ቀንበሬን፣ ቤተሰቤን ጥዬ፣
"እኔም ሜዳ ገባሁ፣ እሱን ተከትዬ፣
"እዚያም ተገናኝተን፣ አብረን ስንዋጋ፣
"ጥሎኝ ሱዳን ገባ፣ ሌሊቱ ሳይነጋ፣
"አሁንም ፍለጋ፣ የተሻለ ሕይወት፣
"ወደዚያ የሄደው፣ ይሆናል በማለት፣
"ድንበር አቋርጬ፣ ዳግም ተከተልኩት፣
"ካርቱም ከተማም ውስጥ፣ ድንገት አገኘሁት፣
"ስለባዕድ ሀገር፣ ኑሮ ስጠይቀው፣
"አጫወተኝና፣ ብዙ እንዳልተመቼው፣
"ያ መንገደኛ ሰው፣
"ምሁር ሊቅ የምለው፣
"እኔ ስከተለው፣ እሱም የሚሄደው፣
"ፈቃድ እንደሰጠው፣ ያሜሪካ መንግሥት፣
"በጣም ደስ ብሎት፣ በነገረኝ ማግሥት፣
"ተሳክቶለት ሄደ፣ ከሱዳን ሸኘሁት፣
"ሲሄድ ስከተለው፣ ዳግም ተለየሁት፣
"የተሻለ ላድን፣ ሄጄ በእሱ ዱካ፣
"እኔም ብዙ ሳልቆይ፣ ገባሁ አሜሪካ፣
"እዚያም ደረስኩና፣ በሰው ሳጠያይቅ፣
"ዳግም አገኘሁት፣ ያን የተማረ ሊቅ፣
"ካገር ቤት ጓደኛ፣ አስመጥቶ፣ አግብቶ፣
“ልጆች ወልዶ ስሞ፣ ጉልቻ መስርቶ፣
"በሚያውቀው ፈረንጅ አፍ፣ ቁጥርጥሩን ፈቶ፣
"ሕይወቱን ይመራል፣ ኑሮን አደራጅቶ፣
"በሱ ፈለግ፣ መንገድ፣ ልቤ መኖር ሽቶ፣
"የልጅነት ሚስቴን፣ ጋሜዋን አምጥቶ፣
"ካሰበው ለመድረስ፣ አቀበቱን ወጥቶ፣
"በጀመረው መንገድ፣ በቋንቋ ታግቶ፣
"ይኸው አንተ መጣህ፣ ቱርጅማን ተጠርቶ፤"
ሲለኝ፣ ሲያጫውተኝ፣
ያ የሀገሬ ሰው፣ እኔን በእሱ አሳየኝ!